# እንኳን ደህና መጡ

በቀጣይ ለሚያደርጉት ሂደት Inova ስለመረጡ እናመሰግናለን፡፡ ደህንነቱ በተጠበቀ ከፍተኛ ጥራት ያለው እንክብካቤ ለማቅረብ እንሰራለን፡፡ በ Inova በፍቅርና እንክብካቤ እናገለግሎታለን፡፡

ይህ መመርያ ለሂደቱ በምን መልኩ እንደሚዘጋጁ፣ ወደ ሆስፒታሉ ወይ የቀዶ ጥገና ማእከል ከመጡ በኋላ ምን እንደሚጠብቁና ሂደቱ ከተጠናቀቀ በኋላ እንክብካቤዎን በምን መልኩ እንደሚያቅዱ መረጃ ያቀርባል፡፡ ተጨማሪ ጥያቄ ካሎት እባክዎትን ቀዶ ጥገና ለሚያካሂደው ወይ ከሂደትዎ በፊት ቃለ መጠይቅ ላደረገሎት የህክምና ቡድን ያናግሩ፡፡

## በዚህ ሰነድ ውስጥ የሚያገኙት

- የመጀመርያ ሂደት
- የቅድመ-ሂደት ግምገማ ቀጠሮ ዎርክሺት
- ሂደትዎ በፊት አስፈላጊ የሆኑ መመርያዎች
- ለሂደቱ ቀን የሚያስፈልጎት አስፈላጊ መመርያዎች
- የመፆም መመርያ
- ከሂደት በፊት የቆዳ ማፅዳት መመርያዎች
- ማገገምና ወደ ቤት መውጣት
- የሂደት ክፍያዎን ሒሳብ መረዳት
- በቦታ አስፈላጊ መረጃ

## የመጀመርያ ሂደት

ለሂደቱ ቀጠሮ ካስያዙ በኋላ፣ እባክዎትን ወደ MyChart በ **inova.org/mychart** በመግባት **አንላይን የህክምና ታሪክ መጠይቅ አንላይን ይሙሉ**፡፡

አዲስ ተጠቃሚ ከሆኑና MyChart ከሌሎት፣ እባክዎትን በ **inova.org/mychart** **አሁን ይመዝገቡ**፡፡ በ MyChart ቴክኒካዊ ችግር ካጋጠሞት እባክዎትን በ855-MYINOVA (855-694-6682) በመደወል ተወካዩን ለማናገር ‹‹4›› ይጫኑ፡፡

MyChart ማግኘት ካልቻሉ በገፅ 3 የሚገኘውን የቅድመ-ሂደት ቀጠሮ ዎርክሽት መሙላት ይችላሉ፡፡ የስልክ ቃለመጠየቅ ቀጠሮ ሲያካሂዱ እባክዎትን ይህን ሰነድ ይዘው ይቅረቡ ወይ ወደ ቅድመ ሂደት ግምገማና ቅድመ-ቀዶ ጥገና ይዘው ይምጡ፡፡

እባክዎትን ቀጠሮ በምንይዝበት ግዜ አስተርጓሚ ካስፈለግዎት ያሳውቁን፡፡

የቅድመ ቀዶጥገና ቃለመጠይቅ አብዛኛው ግዜ 30 እስከ 90 ደቂቃ ይወስዳል፣ ይህም ፍላጎቶን መሰረት በማድረግ በስልክ፣ ቴሌሜዲስን ወይ በአካል ሊካሄድ ይችላል፡፡ አመቺ የሆነ የቀጠሮ ግዜ ለማግኘት እንዲረዳዎት በተቻለ ፍጥነት ቀጠሮ ኣስቀድመው እንዲይዙ እንመክራለን፡፡

**በአድቫንስድ አገልግሎት አቅራቢ ወይ ከነርስ ጋር በስልክ በሚካሄደው ቅድመ ሂደት በቅድመ-ማደንዘዣ ግምገማ ወቅት፣ እኛ የምናደርገው**

- የሜዲካል ታሪክና መድሃኒት ግምገማ
- ከሂደቱ በፊት የሚያስፈልጎት ፈተና መወሰን
- የምርመራ ውጤት መገምገምና ክትትል ስለሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች አስፈላጊ ለሆኑ አቅራቢዎች ማሳወቅ
- አስፈላጊ የሆኑ Inova ሰነዶች፣ ከውጭ የተካሄዱ ምርመራ ውጤቶች፣ የህክምና ታሪክ፣ አካላዊ ምርመራ፣ የፈቃድ ቅፅና አስቀድሞ የሚሞላ መመርያ የመሳሰሉትን ይገመግማል
- ፆምና የመድሀኒት መመርያ ጨምሮ የቅድመ ሂደትና በሂደቱ ቀን ያለው መመርያና ትምህርት
- ጥያቄዎችን መመለስ

**ቅድመ ሂደት ግምገማ ቀጠሮ ቀን፡** ______________________________

**ቅድመ ሂደት ግምገማ ቀጠሮ ሰዓት፡** ______________________________

**ቅድመ ሂደት ግምገማ ቦታ (እባክዎትን አንድ ይምረጡ)**

☐ Inova ቅድመ ሂደት ግምገማ – Alexandria
4320 Seminary Rd.
Alexandria, VA 22304
ስልክ፡ 703-504-7880

☐ Inova ቅድመ ሂደት ግምገማ – Willow Oaks (Fairfax)
8260 Willow Oaks Corporate Dr. #650
Fairfax, VA 22031
ስልክ፡ 703-776-2000

☐ Inova ቅድመ ሂደት ግምገማ – Fair Oaks
3700 Joseph Siewick Dr., #100
Fairfax, VA 22033
ስልክ፡ 703-391-4809

☐ Inova ቅድመ ሂደት ግምገማ – Loudoun
44045 Riverside Pkwy. #165
Leesburg, VA 20176
ስልክ፡ 703-858-8192

☐ Inova ቅድመ ሂደት ግምገማ – Mount Vernon
2501 Parkers Ln.
Alexandria, VA 22306
ስልክ፡ 703-664-7545

## የቅድመ-ሂደት ግምገማ ቀጠሮ ዎርክሺት

**ያለ ሀኪም ትእዛዝ የሚገዙ መድሀኒቶች፣ በሀኪም ትእዛዝ የሚገዙ መድሀኒቶች፣ ቫይታሚን ወይ ኤሌክትሮያልስ ጨምሮ አሁን የሚወስዱት መድሀኒቶች፡**

| የመድሀኒት ስም | የሚወስዱት መጠን | የቀጠሮ ሰዓት |
|---|---|---|
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |

**ከዚህ ቀደም የተካሄዱ ማደንዘዣ የሚፈልጉ ሂደቶችና ቀዶ ጥገናዎች፡**

**የመጀመርያ ደረጃ ሀኪምና ሌሎች ስፔሻሊስቶች ስም፡**

| የሀኪም ስም | ስፔሻሊቲ | ስልክ ቁጥር |
|---|---|---|
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |

## ሂደትዎ በፊት አስፈላጊ የሆኑ መመርያዎች

ቀጠሮዎ ቀን መቀየር ካለበት ወይ ከሰረዙት ቀዶ ጥገና ሀኪሞን ያግኙ፡፡ ከታመሙ ወይ ትኩሳት ካልዎት ለሂደቱ ቀጠሮ ከማስያዞ በፊት እባክዎትን ወደ ቀዶ ጥገና ባለሙያው ይደውሉ፡፡ ሂደቱ እስከሚካሄድበት ቀን አይጠብቁ፡፡

- መታወቅያና መድሕን ካርድ፣ ክፍያ (በቼክ፣ ጥሬ ገንዘብ ወይ ክሬዲት ካርድ)፣ እንዲሁም የፋርማሲ ካርድ ይዘው ይምጡ፡፡
- እቤትዎ የሚያደርስዎትን መጓጓዣ ያመቻቹ፡፡ ለደህንነቶ ሲባል ማድንዘዣ ከወሰዱ በኋላ ራስዎ እንዲያሽከረክሩ ወይ የህዝብ ማመላለሻ እንዲጠቀሙ አይፈቀድሎትም፡፡ ሓላፊነት የሚሰማው አዋቂ ከቤት ወደ ሆስፒታል ሊወስዶት ይገባል፡፡ የህዝብ ማመላለሻ ወይ መኪና መጋራት አገልግሎት የሚጠቀሙ ከሆነ ከሹፌሩ ሌላ አዋቂ ሊኖር ይገባል፡፡ ሂደቱ ከተካሄደ ለመጀመርያ 24 ሰዓት አዋቂ ከእርስዎ ጋር እንዲኖር አጥበቀን እንመክራለን፡፡
- በቀዶ ጥገና ሀኪም ወይ ከሂደት በፊት አቅራቢው የተለየ መመርያ ካልተሰጦት እባክዎትን በገፅ 7 ላይ ያለውን የቆዳ ማፅዳት መመርያ ይተግብሩ፡፡
- ሂደቱ ከመካሄዱ 24 ሰዓት በፊት ፀጉር መላጫ ወይ ፀጉር ማንሻ አይጠቀሙ፡፡
- ሎሽን፣ ሽቶ፣ የሚነፎ ምርቶች ሜክአፐ አይጠቀሙ፡፡
- ሰፊና ምቹ የሆኑ ልብሶችን ይልበሱ፡፡
- እባክዎት ውድ ንብረቶችና ጌጦችን እቤት አስቀምጠው ይምጡ፡፡ ሁሉንም ጌጦችና ቀለበት ያውጡ፡፡
- እባክዎትን ኮንታክት ሌንሶን እቤት አስቀምጠው ይምጡ፡፡ መነፀር የሚያደርጉ ከሆነ መነፀር ማስቀመጫ ይዘው ይምጡ፡፡
- የጆሮ ማዳመጫ የሚያደርጉ ከሆነ፣ እባክዎትን የእርስዎ ስምና የትውልድ ዘመን የተፃፈበት የማዳመጫ ማስቀመጫ ይዘው ይምጡ፡፡
- ኦብስትራክቲቭ የመኝታ ኤፒን ካልዎት Inova ከሂደቱ በኋላ ተቀብሎ ለጊዝያዊ ጥቅም CPAP ክፍል ያቀርባል፡፡ ተመላልሰው እንዲታከሙ ቀጠሮ ከተያዘ የግል CPAP ወይ BiPAP ማሽን ማምጣት ይችላሉ፡፡
- የቅደመ መመርያ፣ ኑዛዜ ወይ ውክልና ቅጂ ካሎት ይዘው ይምጡ፡፡ ቅድመ መመርያ እንዲኖሮት እናበረታታለን፡፡ አስቀድሞ ስለሚሰጥ መመርያ ተጨማሪ ማወቅ ከፈለጉ inova.org/advancedirective ይጎብኙ፡፡
- ታካሚው ስለ ሕክምና ውሳኔ መስጠት ካልቻለ እባክዎትን ተገቢ የሆነ አዋቂ አብሯቸው እንዲመጣና የፍቃድ ቅፅ ላይ እንዲፈርም ያድርጉ፡፡

በቅድመ-ማደንዘዣ ጊዜ የተሰጦትን መመርያ በሚገባ ሊገመግሙና (በMyChart ይገኛል) በሚገባ ሁሉንም መመርያ በተለይም መድህኒትና የፆም መመርያ መከተል አለቦት፡፡

## ለሂደቱ ቀን የሚያስፈልጎት አስፈላጊ መመርያዎች

**እባክዎትን ሂደቱ የሚካሄድበትን ቦታ ይምረጡ፡**

### Inova ሆስፒታል መሰረት ያደረገ የቀዶ ጥገና ቦታ

- ☐ Inova Alexandria Hospital Surgery Center
- ☐ Inova Fairfax Medical Campus Surgery Center
- ☐ Inova Fair Oaks Hospital Surgery Center
- ☐ Inova Loudoun Hospital Surgery Center
- ☐ Inova Mount Vernon Hospital Surgery Center
- ☐ Inova Professional Services Building Surgery Center
- ☐ Inova Women's Hospital Surgery Center
- ☐ Inova Schar Cancer Institute

### Inova ተንቀሳቃሽ ቀዶ ጥገና ማእከል

- ☐ Inova Franconia-Springfield Ambulatory Surgery Center
- ☐ Inova Lorton Ambulatory Surgery Center
- ☐ Inova Loudoun Ambulatory Surgery Center
- ☐ Inova McLean Ambulatory Surgery Center
- ☐ Inova Northern Virginia Ambulatory Surgery Center (Fair Oaks)
- ☐ Inova Woodburn Ambulatory Surgery Center

**ሂደት የሚካሄድበት ቀን፡** ______________________________

**የሚመጡበት ሰዓት፡** ______________________________

**ሂደት የሚካሄድበት ሰዓት፡** ______________________________

## የመፆም መመርያ

ማደንዘዣ ለሚያስፈልጋቸው ሂደቶች ከታች የተዘረዘረውን የፆም መመርያ ይከተሉ፡፡

ከቀዶ ጥገና ሀኪም ወይ የሂደቱ ባለሙያ የቅድመ ሂደት አመጋገብ መመርያ ከደረሶትና ይህም ረዘም ላለ ግዜ እንዲፆሙ የሚል ከሆነ፣ እባክዎትን ይህን መመርያ በሚገባ ይከተሉ፡፡

እዚህ ውስጥ የተገለፁት መመርያዎች አጠቃላይ መመርያዎች ስለሆኑ ለሁሉም ታካሚ የሚመለከት ላይሆን ይችላል፡፡

| ደረቅ | ፈሳሽና አይስ ቺፕ | የጡት ወተት | የጨቅላ ህፃናት ፎርሙላ | የሰው ያልሆኑ ወተቶች |
|---|---|---|---|---|
| ሂደቱ ከመካሄዱ 11 ፒኤም በፊት ምንም ዓይነት ምግብ እንዳይበሉ፡፡ | እንዲመጡ ከተነገሮት 2 ሰዓት በፊት ‹‹ክሊር›› ፈሳሽ ወይ አይስ ቺፕ መውሰድ ይችላሉ፡፡<br><br>ክሊር ፈሳሽ ውሃ፣ አፕል ጭማቂ፣ እንደ Gatorade የመሳሰሉ የስፖርት መጠጦችና ክሬም ወይ ወተት የሌለው ቡና ወይ ሻይ፡፡ ስኳር ወይ ማጣፈዓ መጨመር ይቻላል፡፡ | ሂደቱ ከሚካሄድበት 4 ሰዓት በፊት ጡት ማጥባት መቆም አለበት፡፡<br><br>ሲርያል ወይ ማወፈርያ አይጨምሩ፡፡ | ሂደቱ ከሚካሄድበት 6 ሰዓት በፊት ጡት ማጥባት መቆም አለበት፡፡<br><br>ሲርያል ወይ ማወፈርያ አይጨምሩ፡፡ | ሂደቱ ከሚካሄድበት 6 ሰዓት በፊት ጡት ማጥባት መቆም አለበት፡፡<br><br>ሲርያል ወይ ማወፈርያ አይጨምሩ፡፡ |

## ከሂደት በፊት የቆዳ ማፅዳት መመርያዎች

ሂደቱ በሚካሄድበት ሰውነት ክፍል ላይ የኢንፌክሽን ስጋት ለመቀነስ ሂደቱ ከመካሄዱ በፊት በቤትዎ ውስጥ በልዩ የጀርም ገዳይ ማፅጃዎች ማፅዳት አስፈላጊ ነው፡፡ ሰውነትዎን በ4% ክሎረክስዲን ግሉኮንታ (እንዲሁም CHG በመባል ይታወቃል) በመጠቀም በተገቢ መልኩ ለማፅዳት እባክዎትን የሚከተለውን መመርያ ይከተሉ፡፡

### CHG የት ይገኛል

CHG አንቲማይክዎባያል ለመግዛት መድህኒት ማዘዣ አያስፈልጎትም፡፡ CHG በማንኛውም ፋርማሲ ይገኛል፤ ድጋፍ ለማግኘት ፋርማሲስቱን ወይ ቴክንሻኑን ይጠይቁ፡፡ አንዳንድ CHG ብራንድ ስሞች Hibiclens፣ Hibistat፣ Exidine እንዲሁም Hex-A-Clens ያካትታል፡፡

በእያንዳንዱ ገላዎን በሚታጠቡበት ወቅት ከሁለት እስከ አራት ኦንስ ይጠቀሙ፡፡

### CHG እቤት ውስጥ እንዴት መጠቀም ይቻላል

- ሰውነትዎን ሲታጠቡ CHG ይጠቀሙ፡፡ መታጠብያ ገንዳ ውስጥ እንዳይገቡ፡፡
- ሂደቱ ከመካሄዱ በፊት ያለው ማታና ሂደቱ የሚካሄድበት ጠዋት ላይ ማለትም እቤት ውስጥ ሁለት ጊዜ ሲታጠቡ CHG ይጠቀሙ፡፡
- የመገጣጠምያ ወይ ስፓይን ቀዶ ጥገና እሚያደርጉ ከሆነ፣ CHG ቀዶ ጥገና ከማድረጎ ሁለት ምሽትና ቀዶ ጥገና በሚደረግበት ጥዋት ላይ ባጠቃላይ ሶስት ጊዜ ይታጠቡ፡፡

### CHG በመጠቀም እንዴት ቆዳችንን እናፅዳለን

1. መጀመርያ ምሽት ገላውን ይታጠቡ፣ ሲታጠቡ በማንኛውም ሳሙና ይታጠቡ፡፡
2. CHG ከመጠቀሞ በፊት መደበኛውን ሳሙናና ሻምፖውን ከሰውነቶ እንዳፀዱ ያረጋግጡ፡፡
3. የሻወሩን ውሃ ዘግተው በእጅዎ CHG ሰውነቶን ይቀቡ፡፡ እባክዎትን ፊቶን፣ ፀጉርና መራብያ አካሎትን እንዳይቀቡ፡፡
4. ለሶስት ደቂቃ ሂደቱ የሚካሄድበትን ስፍራ ያፅዱ፡፡ ሂደቱ የሚካሄድበትን ቦታ ማጠብ ካልቻሉ፣ እባክዎትን የሆነ ሰው እንዲረዳዎት ያድርጉ፡፡ እባክዎትን አጋዠ እርስዎን ከመርዳታቸው በፊት እጃቸውን በሚገባ መታጠባቸውን ያረጋግጡ፡፡
5. ቆዳዎ ላይ CHG ተቀብተው ከጨረሱ ከሶስት ደቂቃ በኋላ ውሃውን ከፍተው በሚገባ የ CHG ውህድ ከሰውነቱ ያፅዱ፡፡
6. በንፁህ ደረቅ ፎጣ እራስዎትን በደንብ ያደርቁ፡፡
7. ሎሽን፣ ፓውደር፣ ሽቶ ወይ ዴዶራንት እንዳይቀቡ፡፡
8. ንፁህ ፒጃማ ወይ ልብስ ይልበሱ፡፡
9. CHG ከታጠቡ በኋላ እንስሳ አልጋዎ ላይ ከእርስዎ ጋር እንዲተኛ አናበረታታም ምክንያቱም እንስሳት ለተለያዩ ባክተርያዎች ተጋላጭ ሊያደርጎት ይችላል፡፡
10. የመገጣጠምያ ወይ ስፓይን ቀዶ ጥገና እሚያደርጉ ከሆነ፣ ለሁለተኛ የምሽት ሻወር ሂደት ይድገሙ፡፡
11. ሂደቱ በሚካሄድበት ቀን ገላዎን ሲታጠቡ ከላይ የተጠቀሰውን መመርያ ይከተሉ፣ ነገር ግን መደበኛ ሳሙና ወይ ሻምፖ እንዳይጠቀሙ - CHG ብቻ መጠቀም ይኖርቦታል፡፡

## CHG እና ፀጉር መላጨት

- CHG በቅርብ የተላጨ ሰውነት ላይ ከተቀባ ያቃጥላል፡፡ ሂደቱ ከመካሄዱ ከ24 ሰዓት በፊት ፀጉሮን እንዳይላጩ ወይ መላጫ እንዳይጠቀሙ፡፡
- ከ24 ሰዓት በፊት መላጨትን ከመረጡ እባክዎትን ቆዳዎን እንዳያቃጥሎት ወይ ፀጉር ወደ ሰውነትዎ እንዳይጣበቅ CHG ከመጠቀሞ በፊት ይላጩ፡፡
- ለሂደቱ ፀጉር መላጨት አስፈላጊ ከሆነ በቀዶ ጥገና ክፍል ባሉት የቀዶ ጥገና ቡድን አባላት ይካሄዳል፡፡

## CHG ጥንቃቄዎች

- CHG በመጠቀሞ ሰውነቶ ከቀላ ወይ ካሳከኮት ይህን መጠቀም በማቆም የቀዶ ጥገና ሀኪሞን ያግኙ፡፡
- ለፊትዎ፣ ፀጉርና መራብያ ክፍል CHG አይጠቀሙ፡፡
- ገላ ለመታጠብ CHG ብቻ ይጠቀሙ፡፡ መታጠብያ ገንዳ ውስጥ እንዳይገቡ፡፡ ገላዎን መታጠብ የማይችሉ ከሆነ ተጨማሪ መመርያ ለማግኘት ወደ ቀዶ ጥገና ፅህፈት ቤት ይደውሉ፡፡

# ማገገምና ወደ ቤት መውጣት

- አማካኝ የማገገምያ ግዜ በተለምዶ ከሁለት እስከ አራት ሰዓት ነው፣ ነገር ግን በሚካሄደው ሂደትና የሚኖረው የጎንዮሽ ችግር መሰረት በማድረግ ሊረዝም ይችላል፡፡
- ከመውጣቶ በፊት እርስዎና አስታማሚዎ ከቀዶ ጥገና ባለሙያ መመርያና መድሀኒት ይታዘዝሎታል፡፡ በቤት ውስጥ ማገገም እንዲቀጥሉ ለማድረግ በሚገባ ዝግጁ መሆኖን እናረጋግጣለን፡፡
- ሂደቱን ያካሄዱበት ቦታ ፋርማሲ ካለው ከመውጣቶ በፊት የታዘዘሎትን መድሀኒት እዛው ማስሞላት ይችላሉ፡፡
- እንደ ማስታወሻ፣ ለእርስዎ ደህንነት ሲባል ማደንዘዣ ከተሰጦት በኋላ መኪና ሊያሽረክሩ ወይ ብቻዎን የህዝብ መጓጓዣ እንዲጠቀሙ አይፈቀድሎትም፡፡ ሓላፊነት የሚሰማው አዋቂ ከቤት ወደ ሆስፒታል ሊወስዶት ይገባል፡፡ የህዝብ ማመላለሻ ወይ መኪና መጋራት አገልግሎት የሚጠቀሙ ከሆነ ከሹፌሩ ሌላ አዋቂ ሊኖር ይገባል፡፡ ሂደቱ ከተካሄደ ለመጀመርያ 24 ሰዓት አዋቂ ከእርስዎ ጋር እንዲኖር አጥበቀን እንመክራለን፡፡

## የሂደት ክፍያዎን ሒሳብ መረዳት

ሂደቱ ከመካሄዱ በፊት የ Inova ፋይናንስ አገልግሎት ክፍል የሚከተለውን ያደርጋል፡

- ሽፋኖንና ጥቅሞችን ያረጋግጣል
- ከመድህን ሽፋኖ አስፈላጊ የሆነውን ፈቃድ ያገኛል
- የሚጠበቅቦትን የፋይናንስ ሀላፊነት መረዳት ላይ ያግዞታል
- የፋይናንስ ስምምነት ያዘጋጃል

ልናገኝዎት ካልቻልን እባክዎትን በሂደቱ ላይ ለሚኖረው ማንኛውም የጋራ ክፍያ ወይ የጋራ መድህን ለመክፈል ዝግጁ ይሁኑ፡፡

ኮስመቲክ ሂደት ከተደረገ አስቀድሞ ክፍያ መከፈል አለበት፡፡

**ሂደቱ ከተካሄደ በኋላ የተለያዩ ክፍያዎች እንደሚከፍሉ መጠበቅ አለቦት፡፡**

- ከቀዶ ጥገና ወይ ሂደት ጋር ለሚያያዙ ወጪዎች የቀዶ ጥገና አቅራቢው መጀመርያ ለመድህን አቅራቢዎ ያስከፍላል፡፡
- እንደሚቀነስ ወጪ፣ የጋራ ክፍያ ወይ የጋራ መድህን የመሳሰሉ ተቀንሰው የቀረውን ሒሳብ ይሰጦታል፡፡
- ከቀዶ ጥገና ቡድን አቅራቢዎች የተለያዩ ክፍያዎች ይደርሶታል፡፡ የሚከተሉትን ሊያካትቱ ይችላሉ፡

**የሆስፒታል ክፍያዎች፡**

- ይህ ሂደቱ ወይ ቀዶ ጥገና ለተካሄደበት ሆስፒታል ወይ ቀዶ ጥገና ማእከል የሚከፈል ክፍያ ነው፡፡ ይህ ክፍያም ለሰራተኞች፣ አቅርቦቶችና ለቀረበው የቀዶ ጥገና አገልግሎት መሳርያ ወጪ የሚሸፍን ነው፡፡
- ሒሳቡን የሚመለከቱ ጥያቄዎችና ክፍያዎች በሒሳብ ዝርዝሮ ላይ ወደ ተጠቀሰው ሆስፒታል/ተቋም መላክ አለበት፡፡ ወይ ወደ Inova ታካሚዎች የፋይናንስ አገልግሎት በ 571-423-5750 ይደውሉ፡፡
- ግምት በተመለከተ ጥያቄ ካሎት እባክዎትን ሂደቱ ወደ እሚካሄድበት ቦታ ይደውሉ፡፡ የቡድኑ አባላቶች ከሰኞ-ዓርብ ከ 8:30 ከሰዓት በፊት እስከ 4:30 ከሰዓት በኋላ ሊያግዞት ይችላል፡፡

**የቀዶ ጥገና ሀኪም ክፍያ፡**

- ይህንን ክፍያ ሒሳብ የሚመለከቱ ጥያቄዎች በደረሰኙ ላይ ወዳለው ቀዶ ጥገና ባለሙያ መላክ አለበት፡፡

**የማደንዘዣ ክፍያዎች፡**

- ይህ በሂደቱ ግዜ በማደንዘዣ ባለሙያ ለሚሰጠት የማደንዘዣ ኣገልግሎት የሚውል ክፍያ ነው፡፡
- ይህን ክፍያ የተመለከቱ ጥያቄዎች ካልዎት በሒሳብዎ ላይ ለተጠቀሰውን ማደንዘዣ ቡድን መላክ አለበት፡፡

## በቦታ አስፈላጊ መረጃ

### Inova ቅድመ ሂደት ግምገማ – Alexandria

**4320 Seminary Rd.**
**Alexandria, VA 22304** **703.504.7880**

| | |
|---|---|
| ዋና የሆስፒታል ኦፕሬተር ………………………………...……………. | 703.504.3000 |
| የፋይናንስ ማማከር ………………………………………………… | 703.504.3098 |
| Inova ማእከላዊ የክፍያ ፅሕፈት ቤት ………………………………... | 571.423.5750 |

ከሰኞ እስከ ዓርብ ቀዶ ጥገና ሂደት ወይ ኢንዶስኮፒ ለማካሄድ ቀጠሮ ያላቸው ታካሚዎች መግቢያ በር 6 ይጠቀሙ፡፡ ከገቡ በኋላ እንዲመዘገቡ ጥበቆች ወደ ቀዶ ጥገና ማእከል ወይ ኢንዶስኮፒ ክፍል ያመላክታችኋል፡፡

ሂደቶ ወይ የቀዶ ጥገና ቀጠሮ የተያዘው ለ**ቅዳሜ** ከሆነ፣ እባክዎትን የታካሚ መግብያ - በር 6 በመግባት በድንገተኛ አደጋ ክፍል ይመዝገቡ፡፡ ምዘገባውን ካጠናቀቁ በኋላ ወደ ቀዶ ጥገና ማእከል የምንወስዶት ይሆናል፡፡ እባክዎትን በዚህ ቀን በቀዶ ጥገና እንግዳ መቀበያ ላይ ይቆዩ፡፡

በሀዎርድ መንገድ አጠቃላይ የመኪና ማቆምያ በነፃ ማቆም ይችላሉ፡፡ የሚከፍሉበት የመኪና ማቆምያ ከጠያቂዎች መግብያ አጠገብ ያገኛሉ፡፡ ታካሚዎችና ጠያቂዎች በመኪና ማቆምያው ላይ የተለጠፈውን መደበኛ ክፍያ መክፈል አለባቸው፡፡

ስለ አቅጣጫና መኪና ማቆምያ በተመለከተ ወቅታዊ መረጃ ከፈለጉ እባክዎትን inova.org/iah ይጎብኙ፡፡

### Inova ቅድመ ሂደት ግምገማ – Willow Oaks (Fairfax)

**8260 Willow Oaks Corporate Dr.** **703.776.2000**
**#650**
**Fairfax, VA 22031**

| | |
|---|---|
| ዋና የሆስፒታል ኦፕሬተር ………………………………...…………….. | 703.776.4000 |
| የፋይናንስ ማማከር ……………………………………………..... | 703.776.6019 |
| Inova ማእከላዊ የክፍያ ፅሕፈት ቤት ………………………………… | 571.423.5750 |

የታካሚዎችና ጠያቂዎች ተጨማሪ መኪና ማቆምያ አለ፡፡

## Inova ቅድመ ሂደት ግምገማ – Fair Oaks

**3700 Joseph Siewick Dr., Suite 100** **703.391.4362**
**Fairfax, VA 22031**

| | |
|---|---|
| ዋና የሆስፒታል ኦፕሬተር ……………………………...…………….. | 703.391.3600 |
| የፋይናንስ ማግከር …………………………………………………..... | 703.391.3840 |
| Inova ማእከላዊ የክፍያ ፅሕፈት ቤት ………………………………….. | 571.423.5750 |

በ Inova Fair Oaks Medical Campus ውስጥ ተጨማሪ የታካሚዎችና ጠያቂዎች መኪና ማቆምያ ማግኘት ይችላሉ፡፡

የመንቀሳቀስ ችግር ካለቦትና የአካል ጉዳተኞችን መቆምያ ማግኘት ካልቻሉ፣ በዋነኛ ሆስፒታልን 3580 ህንፃ መሀከል ያለውን ቦታ መጠቀም ይችላሉ፡፡ እባክዎትን የጥሪ ሳጥን አዝራሩን በመጫን የቡድን አባላት ወደ ውስጥ እንዲገቡ ይረዳዎታል፡፡

ስለ አቅጣጫና መኪና ማቆምያ በተመለከተ ወቅታዊ መረጃ ከፈለጉ እባክዎትን inova.org/ifoh ይጎብኙ፡፡

## Inova ቅድመ ሂደት ግምገማ – Loudoun

**44045 Riverside Pkwy.** **703-858-8192**
**#165**
**Leesburg, VA 20176**

| | |
|---|---|
| ዋና የሆስፒታል ኦፕሬተር ……………………………...…………….. | 703.858.6000 |
| የፋይናንስ ማግከር …………………………………………………..... | 703.858.8091 |
| Inova ማእከላዊ የክፍያ ፅሕፈት ቤት ………………………………….. | 571.423.5750 |

ነፃ የታካሚዎችና ጠያቂዎች መኪና ማቆምያ ፓስ ከ Inova Loudoun Hospital ካምፓስ ማግኘት ይችላሉ፡፡

በ Inova Loudoun Hospital ለሂደት ቀጠሮ ያላቸው ታካሚዎች በደቡብ የሆስፒታሉን መግብያ (44045) ምልክቶችን በመከተል በደቡብ የመኪና ማቆምያ ላይ ያቁሙ፡፡

ስለ አቅጣጫና መኪና ማቆምያ በተመለከተ ወቅታዊ መረጃ ከፈለጉ እባክዎትን inova.org/visitloudoun ይጎብኙ፡፡

**Inova ቅድመ ሂደት ግምገማ – Mount Vernon**

**2501 Parkers Ln.**
**Alexandria, VA 22306** **703.664.7545**

| | |
|---|---|
| ዋና የሆስፒታል ኦፕሬተር ……………………………...…………….. | 703.664.7000 |
| የፋይናንስ ማማከር ……………………………………………..... | 703.664.7454 |
| Inova ማእከላዊ የክፍያ ፅሕፈት ቤት …………………………………. | 571.423.5750 |

በ Inova Mount Vernon Hospital ካምፓስ ውስጥ ተጨማሪ የታካሚዎችና ጠያቂዎች መኪና ማቆምያ ማግኘት ይችላሉ፡፡

ስለ አቅጣጫና መኪና ማቆምያ በተመለከተ ወቅታዊ መረጃ ከፈለጉ እባክዎትን inova.org/imvh ይጎብኙ፡፡